# የሰላማዊ ሰልፍ ጥሪ

በአፍሪካ ውስጥ እየተካሄደ ያለውን የመሬት ንጥቅያንና ቅርምትን እናውግዝ!
በተለይም በኢትዮጲያ ውስጥ ከእርሻ መሬት ብቻ አልፎ፣ የቤተ ክርስቲያን እና የገዳሞችን መሬት ጨምር መንግስት በጉልበት እየቀማ ነው.
*ጥንታዊው ለምለም የዋልድባ ገዳም የጥንት ይዞታ፣ የቅዱስ አባቶቻችን አጽም ያረፈበት በሙሉ፣ በቡልዶዘር እየተጠረገ ነው. አባይ ፀሃዩ በሚያዘው "የመንግስት" ስኳር ልማት ለማድረግ ስራው የተጀመረ ሲሆን፣ ይህንንም በመቃወም ባህታውያንና የአካባቢው ህዝብ እንቢ ለገዳማችን እያለ ነው.

*አሁንም በጋምቤላ እና አፋር ክልል በሺ የሚቆጠሩ ዜጎችን በማፈናቀልና መግደል፣ የመሬት ነጠቃው ቀጥሏል.እንዴዚሁም በደቡብ ኢትዮጲያ በጉራ ፈርዳ የዘር ማፅዳት በሺፈራው ሽጉጤ መሪነት በመካሄድ ላይ ሲሆን በብዙ ሺህ የሚቆጠር መሬት አልባ ተደርጎ ሲባረር ቦታውን ለመሸጥ ዝግጅቱ ቀጥሏል.

*በቅርብ ግዜ ብቻ በኢትዮጲያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ይዞታ ስር ባሉ 3 ታሪካዊና ጥንታዊ ገዳሞች (ኡራ ኪዳነ ምህረት፣ አሰቦት እና ዝቋላ) ላይ ፣ መንግስት የእሳት ቃጠሎ ወንጀል ፈፅሟል.
እነዚህም ወንጀሎች የሚፈጸሙት መንግስት የቤተ ክህነት አባላትን አፈናቅሎ መሬቱን በርካሽ ለመሸጥ ሲሆን፣ ገዢዎቹም የተለያዩ አለም አቀፍ ኩባንያዎች ናቸው.

ከእነዚህም ኩባንያዎች በአሜሪካ የሚገኙ፣ ትልቅ ሚና የሚጫወቱ ኢንቨስትመት ባንኮች፣ ፋይናንሻል ድርጅቶች፣ ትላልቅ የእርሻ አምራቾች እና ተደራዳሪዎች የበለጠ መሬት ለመግዛት በ Waldorf Astoria (New York City, NY) April 23-24 ለስብሰባ እየተዘጋጁ ነው. www.globalaginvesting.com

በእዚህ ስብሰባ ላይ የሚወሰኑት ውሳኔዎች በኢትዮጲያ ላይ ብቻ ሳይሆን በአፍሪካም ጭምር ከባድ ተእጽኖ ከመጨመሩም ባሻገር፣ የኢትዮጵያ መንግስት ከእነዚህ ኩባንያዎች ገንዘብ ለመቀበል ባለው ከፍተኛ ፍላጎት፣ ነዋሪ ህዝቦችንና ቤተ ክርስቲያኖችን ማፈናቀላቸውን ይጨምራሉ.

የሰብአዊ መብት ከማያከብር መንግስት ጋር መነገድ ማለት፣ የሃይማኖት ህልውና መነጠቅ እና የዜጎችን ክብር ንግፊያ መደገፍ ማለት ነው!! ይህንን ኢ-ሰባዊ የሆነ የንግድ ተግባር አብረን እንድናወግዝ ዘንድ የእርሶን ትብብር እንጠይቃለን.

መቼ፡ ማክሰኞ April 24 2012 ከጠዋቱ 10፡30 am

የት፡ The Waldorf=Astoria
301 Park Avenue
New York City, NY